# የአሶሳ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ መረጃ



# የአሶሳ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ዲዛይን



የኮሌጁ ገቢ ስፋት 8.316 ሄክታር ወይም 83,160 ስኬር ካሬ ሜትር ስፋት አለው

## መግቢያ

በክልላችን በተለያዩ ጊዜያት ተግባራዊ የተደረጉ የአገልግሎት ማሻሻያ ፕሮግራሞች ቢኖሩም ተገልጋዩ የሚፈልጋቸውን ውጤት አሟልቶ ማስገኘት ያላስቻሉ፤የተገልጋዩን ፍላጎት ያላረኩና ከፍተኛ የአገልግሎት ውጣውረድ የነበረባቸው በመሆኑ በኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ መሰረታዊና ፈጣን ለውጥ ከማምጣት ረገድ በርካታ ጉድለቶች እንደነበሩባቸው ታይቷል፡፡
በመሆኑም አሁን ባለው ውድድር የማያቋርጥ ፤ፈጣን ለውጥና ተልዋዋጭ የተገልጋይ ፍላጎት አቀጣጣይነት መንፈስ፤ የለውጥ አሽከርካሪነት ጋር አብሮ ለመጓዝ እንዲቻል የክልሉ መንግስት ማንኛውም አገልግሎት ሰጪ /ምርት አምራች ተቋማት ተገልጋይ ተኮር፤ፈጣን፤ምላሽ ሰጪ ተለማጭ አደረጃጀትና አሰራር እንዲኖራቸውና በመሰረታዊ ስራ ሂደት ለውጥ ተቃኝተው አገልግሎት እንዲሰጡ መወሰኑ ይታወቃል፡፡
በዚሁም መሰረት ተገልጋይ ተኮር የሆነ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችለውን መሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ሂደትን መሰረት ያደረገ የውጤት ተኮር ስርዓት (BSC) ጥናት አጥንቶ በኮሌጁ ባሉት የስራ ሂደቱ ወደ ሙሉ ትግበራ በመግባት አበረታች የአፈጻጸም ውጤት ማስመዘገብ ሲቻል ነው ፡፡
የውጤት ተኮር ስርዓት የተሟላ ተቋማዊ እምርታ እንዲመጣ ለውጡን ተቀብለው መፈፀም በሚችሉ በሰው ሃይል ማሟላትና አፈጻጸማቸውን በመገምገም የሚገኝበት ደረጃ ለመመዘን የሚያስችል ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ይሆናል፡፡

## ተልዕኮ

የውጤት ተኮር ትምህርትና ስልጠና ስትራቴጅን መሰረት በማድረግ በሙያው ብቁ፣ ስራ ፈጣሪና ታታሪ የሆነ፣ በስነ-ምግባር የታነፀ፣ ቴክኖሎጅን መፍጠር፤መጠቀም፣ ማሸጋገር የሚችል እና የተሟላ የኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎት በመስጠት በምርት ጥራታቸው ተወዳዳሪ መሆን የሚችሉ ኢንተርፕራይዞች እንዲፈጠሩ በማድረግ የክልሉን ብሎም የሀገሪቱን ድህነት ማስወገድና ለማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት አስተዋጽኦ ማድረግ።

## ራዕይ

የክልሉን ማህበረሰብ ገበያው በሚፈልጋቸው የሙያ መስኮችና ደረጃዎች በማሰልጠን የሙያ ብቃታቸው የተረጋገጠ በመካከለኛ ደረጃ የሰለጠነ የሰው ሀይል ማፍራት፣ የቴክኖሎጂ ሽግግርና የኢንዳስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት በመስጠት በ2022 የማህበረሰቡ ችግር ተፈቶ ማየት ።

## ዓላማ

- በኮሌጁ እና በክልሉ ባሉ የስልጠና ተቋማት ደረጃ ስትራቴጂው የጠራ ግንዛቤ እንዲይዝ ማድረግ፤
- በኮሌጁ የተቀመጡ ስትራቴጂካዊ ግቦችና ኢላማዎችን መተግበር ማስቻል።
- እያንዳንዱ የትምህርት ክፍል በግልና በቡድን የእድገትና ትራንስፎርሜሽን በስትራቴጂው እቅድ እንዲመዘን ማስቻልና በውጤት መለካት።

**እሴቶች**

- ስራ፡ ጣሪነት፣
- ውጤታማነት ፣
- ተከታታይነት ያለዉ የሙያ ማሻሻል፣
- የሙያዎች እኩልነት፣
- ችግር ፈችነት፣
- ሙያዊ ሥነ ምግባር፣
- በራስ መተማመን፣
- ስራ አክባሪነት፣
- በጋራ መስራት፣
- የፈጠራ ስራዎችን ማበረታታትና ማዳበር፣
- ጥራት፣
- ፍትሃዊነት (ተደራሽነት)፣
- አሳታፊነት፣
- አርአያነት፣
- የዓላማጽናት፣
- ልቆመገኘትና
- ተመራማሪነት ናቸው፡

# የኮሌጁ አመሰራረት መረጃ

የአሁኑ አሶሳ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ በ1994 ዓ.ም ሲቋቋም የአሶሳ ቴኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ተቋም በሚል ስያሜ በሶስት ት/ት ክፍሎች ማለት (accounting ,secrterial science and office management and purchasing and supply management ) ወደ 50 የሚጠጉ ሰልጣኞችን በመቀበል የቴክኒክና ሙያ ት/ትና ስልጠና በመስጠት የጀመረ ተቋም ነው ። ተቋሙ ወደ ኮሌጅነት ከማደጉ በፊት የት/ት ዘርፎችን በማስፋፋት በ1998 ዓ.ም የክልሉ ት/ቢሮ ከፌደራል ውሃ ሀብት ሚኒስተር ጋር በመተባበር በ3 የውሃ ቴክኖሎጅ ት/ት ክፍሎች ማለትም በአነስተኛ መስኖ ተፋሰስ ( small scale irrigation and drainage) በገጠር መጠጥ ውሃ አቅርቦትና ሳኒቴሽን (rural water supply and sanitation ) እና በኤሌክትሮ መካኒካል (Electro mechanical ) ከክልላችን እና ከጋምቤላ ክልል ሰልጣኞችን ተቀብሎ ወደ 600 የሚሆኑ መካከለኛ ባለሙያዎችን አሰልጥኖ በዘርፉ የሰለጠነ የሰው ሀይል ችግር ለመፍታት ጥረት አድርጓል በማድረግም ላይ ይገኛል ።

- ተቋሙ በት/ት ስልጠና ረገድ በክልሉ ያለውን የመካከለኛ ደረጃ የሰው ሀይል ክፍተት ከማሟላት አንጻር በ2000 ዓ.ም የክልሉ ም/ቤት ወደ ኮሌጅነት እንድያድግ ወሰነ ። በ2003 ዓ.ም የአሶሳ ቴክኒክና ሙያ ትም/ት ስልጠና ኮሌጅ ከነበረበት ደረጃውን በማሻሻሉ የአሶሳ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ተብሎ ተሠየመ።
- ኮሌጁ ከተቆረቆረበት ጊዜ ጀምሮ የስልጠና መስኮችን በማስፋፋትና ለድጋፍና ክትትል ሥራ በሚያመች መልኩ በ4 የሙያ ዘርፎች ማለትም በኢንዱስትራል ቴክኖሎጅ፣በቢዝነስና አይ ሲቲ፣በኮንስትራክሽን ቴክኖሎጅ እና በዋተር ቴክኖሎጅ ተደራጂቷል። ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ በት/ት ስልጠና ስር በ4 ት/ት ዘርፎች የየራሳቸው ፈጻሚ ባለሙያ የተመደበላቸው ቢሆንም በትምህርት ክፍሎች መካከል የመረጃ ልውውጥ በሚፈልገው ጊዜና ወቅት ወደ ሚመለከተው አካል ለማድረስ ክፍተቶችና የሰራተኛ ቁጥጥር በማላላቱ ችግሮች ተስተውሏል።

ስለሆነም ይህንን ችግር ለመፍታት አወቃቀሩን ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ ሙሉ በሙሉ በመቀየር ሀላፍነቱን ወደ ት/ት ስልጠና ክፍልሎች በማውረድ በአሁኑ ሰዓት በ14 ዲፓርትመንት ሰልጣኞችን በመቀበል ስልጠና በመሰጠት ላይ የሚገኝ ኮሌጅ ነው። በአሁኑ ጊዜ ኮሌጃችን አደረጃጀት 1 ዋና ዲን፤ 2 ምትክል ዲኖች (ት/ት ስልጠና አካዳሚክ ም/ዲን ፤የቴክኖሎጅ አቅም ክምችት ሽግግር ም/ዲን) ፤4 ዳይሬክተር

(የፋይናንስ ዳይሬክቶሬት ፤የእ/ዝ/ክ/ግ/ዳይሬክቶሬት፤የውስጥ ኦዲት ክዋኔ ዳይሬክቶሬት እና የሰው ሀብት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት)፤3 ስራ ክፍሎች (የህዝብ ግንኙነት፤የግዥና ንብርት አስተዳደር ኃላፍ እና የስነ-ምግባር መከታተያ) እና በአካዳሚክ ዘርፍ 14 /አስራ አራት/ ዲፓርትመንት ማለትም አካውንትንግ፤ሴክሬታሪ፣ ሆቴልና ቱሪዝም፣ የንጹህ ውሃ አቅርቦት፣ ኤለክትሪክ ሲቲ፣ አይ ሲቲ፣ መስኖ፣ ኤሌክትሮ መካኒካል ቴክኖሎጂ፣ ኮንስትራክሽን፣ሰርቬይንግ፣ አውቶሞቲቭ፣ ሜታል ማንፋክቸሪንግ ቴክኖሎጂ ፣ ብውልድግ ኢልክትሪካል ኢንስታሌሽንና ውድወርክ ቴክኖሎጅ የተዋቀር ነው፡፡ በአጠቃላይ ኮሌጁ በ17 የሙያ ዘርፎች ስልጠና እየሰጠ የሚገኝ አንጋፋና ልምድ ያለዉ ኮሌጅ ነዉ፡፡